# ክስ መስማት በኢትዮጵያ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች፡- ሕጉና አተገባበሩ

*ቴዎድሮስ ምህረት*[*]

***አህፅሮተ-ፅሁፍ***

*የፍትሐ ብሔር ክስ ከሚያልፋባቸው ሂደቶች አንዱ ክስ መስማት ሲሆን ይህም በጽሑፍ የቀረበውን ክርክር ቅርጽ ለማስያዝ እና ቀጣዩን አቅጣጫ ለመወሰን የሚረዳ ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚከናወነው ተግባር በፍርድ ቤቱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር መሆን ያለበት ሲሆን ክርክሩን ፈር ለማስያዝ ወሳኙ ሥራ የሚከናወንበት ሂደት ነው፡፡ ይህ ጽሑፍ ሕጉ ይህንን የፍትሐ ብሔር ክስ ሂደት ምዕራፍ በአግባቡ አልሰየመውም፤ በተግባርም በፍርድ ቤቶች የሚታየው የተዘበራረቀ አተገባበር በዚህ ደረጃ ሕጉ ሊያሳካ ያሰበውን ግብ እውን ማድረግ አላስቻለም በሚል ይከራከራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አተገባበሩ መዘበራረቁ በፍርድ ቤቱና በባለጉዳዩች የጊዜና የሀብት ብክነትን እያስከተለ ከመሆኑም በላይ በውሳኔዎች ጥራት ላይ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡ ከዚህም በላይ በሕጉ የተመለከተውና በተግባር በሚታየው አሠራር መካከል ያለው ክፍተት ሂደቱ ተገማች እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ጽሑፍ ሕጉንና አተገባበሩን በመፈተሽ የመፍትሔ ሐሳብ ለማቅረብ ያለመ ነው፡፡*

***ቁልፍ ቃላት፡-*** የመሰማት መብት፣ ክስ መስማት፣ ክርክር መስማት

## *መግቢያ*

በኢትዮጵያ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍትሐ ብሔር ክርክሮች የሚመሩት በ1958 በወጣው የፍትሐ ብሔር *ሥነ-ሥርዓት* ሕግ መሰረት ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር *ሥነ-ሥርዓት* ህጉ በዚህ ዘመን ለሚጠበቀው የፍትሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደር ብቁ ስለመሆኑ ጥያቄ ሊነሳ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በይዘቱ ሕጉ በአመዛኙ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን በአተገባበር ሂደት መዛነፎች ሲያጋጥሙ ይስተዋላል፡፡ መዛነፉ በአንድ ዳኛ የተፈጸመ ወይም በአንዳንድ አጋጣሚ የሚፈጠር ሲሆን ጉዳቱ የጎላ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ችግር በመደበኛነት የሚከሰት ከሆነ ወይም ሕጉ በዘፈቀደ የሚተገበር ከሆነ የሂደቱን ፍትሐዊነት እንዲሁም የውጤቱን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል፡፡ ከዚህም በላይ የዚህ ችግር መኖር የፍትሐ ብሔር *ሥነ-ሥርዓት* ሕጉ ያነገበውን ፍትህን ወጪ ቆጣቢ በሆነና በአጭር ጊዜ የማስተዳደርን ዓላማ ይስታል፡፡ ከዚህ አንጻር ፍርድ ቤቶች በ*ሥራ* ላይ ያለውን ሕግ ለመተግበር መትጋት እንዲሁም አላሰራ የሚሉ ሕጎች ወይም ድንጋጌዎች ደግሞ እንዲሻሻሉ የሕግ ማሻሻያ ሐሳብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡[1]

የፍትሐ ብሔር *ሥነ-ሥርዓት* ሕጉ ከወጣበት ከ1958 ጀምሮ ከፍርድ ቤት *ሥ*ልጣን ጋር በተያዘ ካልሆነ በስተቀር የተደረገ ማሻሻያ እምብዛም ሲሆን የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ክርክር አመራርን በተመለከተ የተደረገ ለውጥ የለም፡፡ የጉዳዮች ብዛትና ውስብስብነት

---

[*] ጠበቃና የሕግ አማካሪ፡፡

[1] *የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ* ቁጥር 25/1988፣ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 13፣ የካቲት 7 ቀን 1988 አንቀጽ 33/2፡፡ በተለይ አንቀጽ 38 *ሥነ-ሥርዓትን የሚመለከቱ መመሪያዎችን እንዲያወጣ ሥ*ልጣን እንደሰጠው ማየት ይቻላል፡፡ *የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ* ቁጥር 454/1997፣ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 11ኛ ዓመት ቁጥር 42፣ ሰኔ 7፣ 1997፡፡

ቢጨምርም፤ በልምድም ሆነ በሕግ አስተምህሮት የተደረሰባቸው አዳዲስ አስተሳሰቦች እና ምክረ-ሐሳቦች ቢኖሩም እስከ አሁን እያገለገለ ያለው በ1958 የወጣው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው ሕግ ታሳቢ ያደረጋቸው ሁኔታዎች በተለወጡበት ሁኔታ እስከአሁን በሥራ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፍትሐ ብሔር ክርክር ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ያለውን ሂደት የሚመለከቱ ቢሆንም በዚህ ጽሑፍ ለማየት የሚሞከረው የመሰማት መብት መገለጫ የሆነውን የክስ መስማት ሂደትን ነው፡፡ የጽሑፉ ትኩረትም አሁን ያለው ሕግ በዚህ የክስ ሂደት ደረጃ ላይ ያለው አቋም፣ ለማሳካት ያሰበውን ግብ እና በፍርድ ቤቶች ያለውን ተፈጻሚነት ለመዳሰስ ነው፡፡

ይህ ጽሑፍ በዋናነት የአንድ ባለሙያ የዓመታት አስተውሎትን (observational study) መሠረት አድርጎ ሕጉና አተገባበሩ ላይ ፍተሻ የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪም በተቻለ መጠን በፍርድ ቤቶች ያለውን አተረጓምና ተዛማጅ የሆኑ አገሮች ተሞክሮ ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ጽሑፉ በዋናነት በፍርድ ቤቶች የሚታየው የተዘበራረቀ አሰራር መልክ መያዝ ስላለበት ወደ መፍትሄው የሚያደርሰንን ውይይት ማስጀመር እንደ ግብ ይወሰዳል፡፡ ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ ባለሙያዎች ያጠራቀሙትን ትዝብት እና ያስተዋሉትን ተሞክሮ ለማጋራት ይነሳሳሉ ብሎ ጸሐፊው ያምናል፡፡ መሬት ላይ ያለው እውነትና የሕጉ አተገባበር በየዕለቱ በሰዎች ኑሮ ላይ ያለውን ውጤት እንዲሁም በፍትህ ሥርዓቱ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መመርመርና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የመጠቆም ኃላፊነት በሁሉም ባለሙያ ላይ የተጣለ ስለሆነ ችግሮችን ለመፍታት መንገዱን በማሳየት ሁሉም ያቅሙን ሊያዋጣ ይገባል፡፡ ይህ ጽሑፍም በዚህ እሳቤ የተደረገ ሙከራ ነው፡፡ ጽሑፉ የመሰማት መብትን ከመመርመር ጀምሮ የክስ መስማትን ምንነትና ዓላማ እንዲሁም ሂደቱንና በዚህ ረገድ በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የክስ አሰማም ዘይቤዎችን በመዳሰስ ወደ ማጠቃለያው ይሄዳል፡፡

## 1. የመሰማት መብት

መንግሥት ካለበት ኃላፊነት በዋናነት በህብረተሰብ ውስጥ ሥርዓት ማስከበር አንዱ ሲሆን ለዚህ ተግባር ከሚያስፈልጉት ተቋማት አንዱ አለመግባባትን የሚፈቱ አካላት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ተቋማት ውሳኔ ለመስጠት መሠረት ከሚያደርጓቸው መሠረታዊ ሕጎች በተጨማሪ ሥራቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚመሩበት የሥነ-ሥርዓት ሕግ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሥነ-ሥርዓት ህግ ከጉዳዩ መጀመር እስከ መጠናቀቅ ያሉ ሂደቶችን በሙሉ የሚገዛ ነው፡፡ አገሮች የዚህን ሕግ ይዘት የመወሰን ስልጣን ያላቸው ቢሆንም የተወሰኑ ሊጣሱ የማይችሉ የተፈጥሮ ሕግ ተደርገው የሚወሰዱ መርሆዎች እንዳሉ ምሁራን ይስማማሉ፡፡[2] በዚህ ደረጃ ከሚመደቡት መብቶች ውስጥ አንዱ ተከራካሪ ወገን መሰማት አለበት (*audi alteram partem* □□□□□□□ □□□□ "let the other side be heard as well") የሚለው መርህ ነው፡፡ ይህ የዓለማዊ እውቀት ብቻ

[2] ለምሳሌ Ajay R. Singh, *Legal Maxim: Audi Alteram Partem & Nemo Judex in Re Sua: Doctrine of Natural Justice*, available at: <https://ctconline.org/documents/legal> (Last accessed December 2018) ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ጽሑፍ የተፈጥሮ ፍትህ ሁለት ሐሳቦችን እንደያዘ ተገልጧል፡፡ ይኸውም ከመሰማት መብት በተጨማሪ አንድ ተከራካሪ ወገን በራሱ ጉዳይ ዳኛ መሆን የለበትም የሚለውን ያካትታል፡፡

ሳይሆን መንፈሳዊ መሠረትም እዳለው ይታመናል። ለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ[3] አዳምና ሄዋን ከገነት ከመባረራቸው በፊት አዳም አታድርግ የተባለውን ማድረጉ ታውቆ ለምን እንዳደረጉ እንዲያስረዱ እድል የተሰጣቸው መሆኑ ይጠቀሳል። ይህ መርሕ በሕግ አስተምህሮት ካለው ቦታ በተጨማሪም በአለም አቀፍ ስምምነቶችም እውቅና ተሰጥቶታል። ለአብነት ለመጥቀስም ዓለም ዓቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 10 በሰዎች መብት እና ግዴታ ላይ ውሳኔ ለመስጠት በግልጽ ችሎት የመሰማት መብት መከበርን እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል።[4] የአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች ቻርተርም (African Charter on Human and Peoples' Reights) እንዲሁ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ሊሰማለት እንደሚገባ ይደነግጋል።[5]

ስለዚህ የአንድን ሰው መብት የሚነካ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ይህ ሰው የመሰማት እድል ሊሰጠው ይገባል። የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ይህ በማንኛውም ሕግ ሊጣስ አይገባም ተብሎ በሕግ አስተምህሮት እውቅና የተሰጠው መርህ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም ሆነ በታሪካዊ የሕግ ሰነዶች ከፍተኛ ቦታ የተቸረው የመሰማት መብት አተገባበርን ማየት ነው። ይህ መብት በፍርድ ቤትም ሆነ በሌሎች በሰዎች መብት ላይ ውሳኔ በሚሰጡ አካላት (quasai-Judicial and administrative organs) መከበር እንዳለበት ግንዛቤ ያለ ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ግን መርሁ በፍርድ ቤቶች በተለይ በፍትሐ ብሔር ጉዳዮች የመዳኘት ሂደት ያለው አተገባበር ነው። የመሰማት መብት በዋናነት በክስ መስማት ሂደት የሚተገበር ሲሆን የዚህ ጽሑፍ ትኩረትም በዚሁ የፍርድ ሂደት ደረጃ ላይ ይሆናል። አንድ ሰው በክስ ሂደት የመሰማት መብቱ ተጠብቋል ሊባል የሚችለው ምን ሂደት ሲሟላ ነው የሚለው ጥያቄ በውጤቱ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ የሚኖረው ቢሆንም ለማየት የምንሞክረው ግን የሂደቱን የተወሰነ ክፍል ነው። ይህን የክርክር ሂደት ደረጃ ክስ መስማት ብለን ብንጠራውም አንድ ዓይነት ስያሜም ሆነ አረዳድ የለም። ይህም በዋናነት በሕጎችም ሆነ በዕለት ተዕለት ሙያዊ ኑሯችን ለስያሜው አንድ ዓይነት አጠቃቀም ስለሌለንና ተመሳሳይ ትርጉም ስለማንሰጠው ነው። በተለይ አብዛኛውን ጊዜ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ጋር አያይዞ የመጠቀም፣ ከአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ጋር የማጣመር እንዲሁም በፍትሐ ብሔር ጉዳዮችም መሰማት በሁሉም የፍትሐ ብሄር ጉዳይ ሂደቶች ጋር ተያይዞ የሚነሳ መሆኑ በጽንሰ ሐሳቡ ላይ እንዲሁም በቃላት አጠቃቀም ረገድ ወጥነት እንደሌለ ማሳያ ስለሆነ ትንሽ ጠለቅ ብሎ ማየትን

[3] በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 13 ላይ ‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሴቲቱን ይህን ያደረግሽው ለምንድነው? አላት›› ተብሎ ተጽፎዋል።

[4] Article 10 of the Universal Declaration of Human Rights reads: "Everyone is entitled in full equality to a fair and public hearing by an independent and impartial tribunal, in the determination of his rights and obligations and of any criminal charge against him."

[5] Article 7 (1) of the African Charter on Human and Peoples' Rights reads:

> Every individual shall have the right to have his cause heard. This comprises: (a) the right to an appeal to competent national organs against acts of violating his fundamental rights as recognized and guaranteed by conventions, laws, regulations and customs in force; (b) the right to be presumed innocent until proved guilty by a competent court or tribunal; (c) the right to defense, including the right to be defended by counsel of his choice; (d) the right to be tried within a reasonable time by an impartial court or tribunal. (Adopted 27 June 1981, OAU Doc. CAB/LEG/67/3 rev. 5, 21 I.L.M. 58 (1982), entered into force 21 October 1986)

ይጋብዛል፡፡ ነገር ግን ከጽሑፉ ወሰን አንጻር በፍትሐ ብሔር ጉዳይ በፍርድ ቤቶች በሚደረገው ክስ መስማት ላይ በማተኮር የቃሉ አጠቃቀምና የመብቱ አተገባበር በዝርዝር ይታያል፡፡

## 2. ክስ መስማት ምንድነው?

ክስ መስማት የፍትሐ ብሔር ክስ ሲከፈት የሚከናወን የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ክስ መክፈት ተብሎ የሚታወቀው የፍርድ ሂደት የትኛው ነው የሚለውን ማየት ይገባል፡፡ ይህን ለመረዳት በሚደረግ ጥረት ተግዳሮቱ የሚጀምረው ከቃላት አጠቃቀም ወጥነት አለመኖር ነው፡፡ ክስ መክፈት፣ የመጀመሪያ ቀጠሮ፣ የቃል ክርክር እንዲሁም ክስ መስማት እና የመጀመሪያ ክስ መስማት የሚሉት ሐረጎች ተመሳሳይ ነገር ለመግለጽ የሚውሉ ቢሆንም በሕጉ ያላቸው አገባብ ወይም በባለሙያዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ ወጥ ካልሆነ በሕግ አተገባበር ላይ ችግር ማስከተሉ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ በችሎት ተደጋጋሚ ሙግት ምንጭ ሲሆን የሚስተዋለው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137 የሚናገረው የመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ (at the first hearing of the suit) የሚለውን አገላለጽ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን አንቀጽ መሠረት አድርጎ ሰነድ ይዞ የሚቀርብ ተከራካሪ ወገን በትክክለኛው በዚህ ድንጋጌ መጠቀም የሚችለው በየትኛው ቀጠሮ ሲቀርብ መሆኑን አስመልክቶ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህም የመጀመሪያውን ቀነ ቀጠሮ መለየትንና ከሌሎች ስያሜዎች ጋር ያለውን አንድነት መመርመርን አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ በአጠቃላይ ለቀረበው ክስ መልስ ከተሰጠ በኋላ ባለው የክርክር ሂደት ደረጃ ስያሜ ላይ ግልጽነት የለም፡፡

በተለምዶ የቃል ክርክር ተብሎ የሚታወቀውና በሕጉ ክስ መክፈት፣ ክስ መስማት፣ የመጀመሪያ ቀጠሮ እና ተከራካሪዎችን መመርመር በሚል የተጠቀሱት አገላለጾች አንድነትና ልዩነታቸውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ የፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ በውስጡ ላለው ለአራተኛው መጽሐፍ፣ ምዕራፍ ሁለት የሰጠው ስያሜ ክስ መስማት (Trial of Suits) የሚል ነው፡፡ የዚህ ምዕራፍ ክፍል አንድ ክስ ሲከፈት ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዓት (Procedure at First Hearing) የሚናገሩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ክፍል ሁለት ደግሞ ክርክሩን መስማትንና ምስክሮችን መመርመርን (Hearing of Suits and Examination of Witnesses) የሚገዙ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው፡፡ ክስ መስማት የሚለው አጠቃላይ ርዕስ የመጀመሪያውን ክስ መስማትም ሆነ ክርክሩን መስማት የሚያጠቃልል ቃል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ በእንግሊዝኛው ከተሰጠው ስያሜ አንጻር የመስማት ሂደቱ በተለያዩ ቀጠሮዎች ለተለያየ ዓላማ የሚካሄድ ሲሆን የሚጀመረውም በክስ መስማት ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ክስ እና ክርክር መስማት ተብለው የሚታወቁት መልስ መቅረብን ተከትሎ በተከታታይ የሚካሄዱ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ሂደት ደረጃዎች ቢሆኑም በሕጉ ክስ መስማት በሚል ተጠቃለዋል፡፡

በዕለት ተዕለት አጠቃቀም የቃል ክርክር የሚለውን አገላለጽ በሕጉ ክስ መክፈት፣ ክስ መስማት እና ተከራካሪዎችን መመርመር ከሚሉት ስያሜዎች ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በነዚህ ስያሜዎች ልዩነትና አንድነት ላይ ምልከታ ሲደረግ ክስ መስማት በአንድ ቀጠሮ ሊያልቅ የማይችል ሰፊ ሂደት ሲሆን ተከራካሪዎችን መመርመር ግን በመጀመሪያው ቀጠሮ የሚከናወን የክስ መስማት አካል ነው፡፡ የመጀመሪያ ቀጠሮ የሚለው አገላለጽም ክስ ለመስማት የተያዘውን ቀጠሮ ለመግለጽ

የሚያገለግል ሲሆን ይህም ተከራካሪ ወገኖችን መመርመርንና ክሱን ለመስማት የተያዘውን የመጀመሪያ ቀጠሮ የሚመለከት ነው፡፡ ሕጉ ክስ መክፈት በሚል የሚገልጸው ክስ መስማትን እንደሆነ ከሕጉ ይዘት ለመረዳት አያዳግትም፡፡ እነዚህ ሐረጎች አንድ ዓይነት ነገር ለመግለጽ ያገለገሉ ከሆነ ወጥ የትርጉም አጠቃቀም እንዲኖርና ወጥ አረዳድ እንዲሰፍን ማድረግ የሚጠበቅበት ሕግ ለምን የዚህ ዓይነት ግርታን በሚፈጥር መልክ መቅረብ እንዳስፈለገ ግልጽ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ይህን ሂደት በገቢር መለየት የማያዳግት ቢሆንም ለይቶ ለመጥራ የሚያስችል ወጥ የሙያ /የቴክኒክ/ ቃል ወይም ሐረግ ሕጉ አለመጠቀሙ እና አሻሚ የቃላት አጠቃቀም የሕጉ መገለጫ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለውን የግንዛቤ ችግር ከቋንቋ የእድገት ደረጃ ወይም ከቃላት ትርጉም ውስንነት ጋር ብቻ ማያያዝ ተገቢ አይሆንም፡፡ የሕጉ ምንጭ ተድርጎ በሚወሰደው የሕንድ የፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግም ተመሳሳይ ችግር እንዳለ ከሚከተለው ገለጻ መረዳት ይቻላል፡፡

> *In fact, there are several judicial pronouncements to the effect that the "first hearing" of a suit would be the point where preliminary examination of a party takes place and when issues are settled/framed. However, there is an inherent contradiction in that position, in as much as, both are distinct events, and cannot possibly take place at the same point, i.e., the "first* hearing".[6] *(በእርግጥ የመጀመሪያው ክስ መስማት ተከራካሪ ወገኖች የሚመረመሩበት እንዲሁም ጭብጥ የሚለይበት ደረጃ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ ፍርዶች አሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሁለት ኩነቶች በአንድ ጊዜ ሊከሰቱ የማይችሉ ስለሆኑ ይህ አቋም በውስጡ ተቃርኖ የያዘ ነው)*

በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የመጀመሪያው ክስ መስማት ተብሎ የሚታወቀው ተከራካሪ ወገኖች የሚመረመሩበት፣ ክስና መልስ የሚነበብበትን እንዲሁም የእምነት/ክህደት ቃል የሚጠየቅበት መሆኑ በሕጉ ቁጥር 241(1) ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ክንውኖች የክስ መስማት አካል መሆናቸው ግለጽ ቢሆንም ጥያቄው እነዚህ ሁሉ በአንድ ቀጠሮ (በክስ መክፈት ወቅት ወይም በመጀመሪያው ቀጠሮ) የሚከናወኑ መሆን አለመሆናቸው ነው፡፡ ከፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ (Civil Procedure Code) አወቃቀር ለመረዳት እንደሚቻለው ክስ መስማት በቀረቡ መቃወሚያዎች ላይ ውሳኔ መስጠትንና ጭብጥ መለየትንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከዚህ ተከትሎ የሚመጣው ክርክሩን መስማት ነው፡፡ ስለዚህ ክስ መስማት በአንድ ቀጠሮ የሚገደብ ሳይሆን በርካታ ቀጠሮዎችን የሚያካትት የሚያከራክር ነጥብ ካለ ደግሞ ጉዳዩን ለክርክር መስማት የማዘጋጀት ዓላማ ያለው ነው፡፡ በአንድ ጸሐፊ በአጭሩ እንደተገለጸው የመጀመሪያው ክስ መስማት ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ነጥብ ለመረዳት ወደ ማመልከቻዎች ይዘት (ክስና መልስ) የሚገባበት ነው፡፡[7] ነገር ግን አከራካሪ ነጥብ በሌለበት ሁኔታ የመጀመሪያው ቀጠሮ የትኛው እንደሆነ መለየት

[6] Avin Chhangani, *OPINION: First hearing of a suit – Need to amend the Code of Civil Procedure*, available at: <https://theindianjurist.com/2018/04/24/opinion-first-hearing-suit-need-amend-code-civil-procedure/>, last accessed: December 2018.

[7] C.K. TAKWANI, CIVIL PROCEDURE 182 (Eastern Book Company, 4th ed., 1997).

ይጠይቃል፡፡ ጭብጥ መያዝ በማያስፈልጋቸው ጉዳዩች[8] የመጀመሪያ ክስ መስማት ተብሎ የሚወሰደው ክርክሩን ለመስማት የሚሰጠው ቀጠሮ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡[9]

## 3. የክስ መስማት ዓላማ

ከላይ እንደተገለፀው የክስ መስማት ዋና ዓላማ ተሟጋቾቹን የሚያለያያቸውን ወይም የሚያከራክራቸውን ነጥብ መለየት ነው፡፡ ይህም የተከራካሪዎችን የእምነት/ክህደት ቃል በመቀበል እና ተከራካሪዎቹን በመጠየቅ የሚያከራክራቸውን ጉዳይ አንጥሮ በማውጣት የሚከናወን ነው፡፡ አንድ ጸሐፊ እንዳስቀመጠው

> *The rule confers on the court a power to examine parties with a view to ascertaining the real points in controversy between them and to get admissions from them, so as to eliminate irrelevant issues and evidence and thereby shorten the trial.*[10] *(ይህ ድንጋጌ ተከራካሪዎችን በመመርመር እና የእምነት ቃል በመቀበል ትክክለኛ የክርክር ነጥቦችን በመለየት አላስፈላጊ ጭብጦችን እና ማስረጃዎችን በማስወገድ ክርክሩን የማሳጠር ስልጣን ለፍርድ ቤት ይሰጣል፡፡)*

ሌላ ተንታኝ ደግሞ ግቡ የተከራካሪ ወገኖች ቅድመ-ምርመራ መሆኑንና የቃል ክርክር የሚያገለግለው ክስና መልሱን ለማሟላት መሆኑ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡[11]

ክስ መስማት ግብ አድርጎ የሚነሳው ተከራካሪ ወገኖች የሚሟገቱበትን ጉዳይ መለየት ነው፡፡ ይህንን ተከራካሪዎቹ ካቀረቡት የጽሑፍ ማመልከቻ (በዋናነት ክስና መልስ) እንዲሁም በክስ መስማት ወቅት ከሚሰጡት ምላሽ ነው፡፡ የሂደቱ ውጤትም ጭብጦቹን መለየት ነው፡፡ ስለዚህ ክስ መስማት አከራካሪውን ነጥብ እና ጭብጡን ለመለየት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በአጭሩ ክስ መስማት ዋናውን ጉዳይ በመለየት በዝርዝር ከቀረበው ጉዳይ አከራካሪውን ነጥብ በመለየት በቀጣይም ውሳኔ የሚሹ ጭብጦችን እና መሰማት ያለባቸውን ማስረጃዎች ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ሁኔታ ፍርድ ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ የሚያውለውን ሀብት እና ጊዜ ለመቀነስ እንዲሁም ውሳኔ በፍጥነት ለመወሰን የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በክሱና በመልሱ ሰፊ ዝርዝር ቢቀርብም የፍርድ ቤቱም ሆነ የተከራካሪዎች ትኩረት መሆን ያለበት በልዩነት ነጥብ ላይ ነው፡፡ ይህም የፍርድ ቤቱን ሥራ ለመቀነስ (ለምሳሌ በክርክር መስማት ጊዜ የሚጠሩትን ምስክሮች ለመወሰን) ይረዳል፡፡ በእርግጥ ክስ ወይም መልስ ሲቀርብ በሚያያዘው የማስረጃ ዝርዝር የሚጠቀሱት ምስክሮች ምን እንደሚያስረዱ በማይገለጽበት እና ቢገለጽም በአብዛኛው ‹‹እንደ ክሱ ያስረዳሉ›› እየተባለ መጥቀስ በተለመደበት ሁኔታ ጭብጡ ቢለይም የትኛው ምስክር በምን ላይ እንደሚያስረዳ ስለማይመለከት ሁሉም ምስክሮች መጠራታቸውን፤ ምናልባትም መሰማታቸውን ማስቀረት አይቻለም፡፡ ስለሆነም የሀብትም ሆነ የጊዜ ቁጠባን ማድረግ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን ክስ ሲቀርብ ምስክር መዘርዘር ብቻ ሳይሆን የሚመሰክሩበትን

8 የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246/2 በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

9 Mayank Shekhar, *Civil Procedure: First Hearing*, LEGAL BITES: LEGAL AND BEYOND, available at <https://www.legalbites.in/first-hearing/> Last accessed on 22/08/2018.

10 P. M. BAKSHI, MULLA CODE OF CIVIL PROCEDURE, 811 (Butterworths, Abridged 13th ed., 2000).

11 Takwani, *supra* note 7, at 182.

ነጥብም ለይቶ የማመልከት ግዴታ[12] ተፈጻሚ ማድረግ ነው፡፡ እንዲህ ከተደረገ ጭብጡ ከተለየ በኋላ ጭብጡን በሚመለከት ነገር ላይ የሚያስረዱትን ምስክሮች ብቻ በመለየት መስማት ይቻላል፡፡ ይህም አለአግባብ የሚጠሩ ምስክሮችን እንግልት፣ የጊዜ ብክነትን እና ወጪን ይቀንሳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአላስፈላጊ ክርክር ዋናው ፍሬ ነገር ሊደበቅ የመቻሉንና ውሳኔውን የተሳሳተ የማድረጉን አጋጣሚ ይቀንሳል፡፡

ጉዳዩን ወዲያውኑ ለመወሰን የሚያስችል የተከሳሽ ወገን እምነት ከሌለ ክስ መስማት ጭብጥ ለመለየት ይረዳል፡፡ ጭብጥ ደግሞ የክርክሩ ወይም የጉዳዩ የጀርባ አጥንት ሲሆን ለክርክሩም ሆነ ለውሳኔው መሠረት ነው፡፡[13] ስለዚህ ክስ የመስማቱ ሂደትና ውጤቱ (የሚመሠረተው ጭብጥ) የቀጣዩን ሂደት አቅጣጫ እና የውሳኔውን ውጤት የሚወስን የክርክር ሂደት ደረጃ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚሰራው ስህተት ቀጣይ ሂደቶችንም ሆነ ፍርዱን የማዛባት ውጤት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን በፍርድ ቤት ከሚሰጡት ውሳኔዎች መረዳት የሚቻለው ጭብጥ መለየት ከባድ ሥራ እንደሆነ ነው፡፡ ይህም በውሳኔዎች ላይ ጭብጥ ተብለው የሚለዩትን በመመርመር የሚደረስበት ድምዳሜ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ከሥራ አለአግባብ ተሰናበትኩ ያለ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ተከሳሽ ቢክደው የሚያዘው ጭብጥ በአብዛኛው 'ከሥራ መሰናበቱ ሕጋዊ ነው አይደለም?' የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ጭብጥ መሆን ያለበት ለምሳሌ የሥራ ስንብቱ መነሻ ‹‹ከስራ ቀርቷል›› የሚል ቢሆን እንደሚነሳው ፍሬ ነገር የተጠቀሰው ምክንያት ከሥራ ለማሰናበት የሚያበቃ መሆኑ ወይም የሚያከራክራቸው ከሥራ መቅረት አለመቅረት ወይም የቀረበትን ምክንያት ከሆነ ይህ ነጥብ ተለይቶ በጭብጥነት መያዝ አለበት፡፡ የውል አለመፈጸም በተመለከተ ደግሞ ውሉ በአግባቡ ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው ሰፊ ጥያቄ ሳይሆን ከሚሰጠው መልስ አንጻር ከውል መኖር አለመኖር ጀምሮ መፈጸም ወይም ላለመፈጸም የቀረበው መከላከያ ተደርጎ ጭብጡ መያዝ አለበት፡፡ በዚህ መሠረት ጭብጥ መሆን ያለበት በደፈናው በውሉ መሠረት ‹‹ፈጽሟል/አልፈጸመም›› በማለት ሳይሆን ከአፈጻጸሙ ጋር ተያይዞ የሚያከራክረው ዋናው ነጥብ ተለይቶ ነው፡፡ ስለዚህ ጭብጥ መያዝ ማለት ሁለቱን ተከራካሪ ወገኖች ያለያየ አንድ ጥያቄ ነጥሎ ማውጣት ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡

በእርግጥ በሕጉ ጭብጥ የሚባለው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነው ሌላኛው ወገን የካደው የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ነጥብ እንደሆነ ይገልጻል፡፡[14] ጭብጥ ለጉዳዩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡[15] እንዲሁም የሚያዘው ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆን ያለበት ሲሆን ይህም የሚወሰነው ለከሳሹ መብት ለመመስረት የሚያስችልና ለተከሳሹ መከላከያ መሆን የሚችል ማናቸውም በሕግ ወይም በማስረጃ የተደገፈ ፍሬ ነገር መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡[16] ጭብጥ የሚነሳው ተከራካሪ ወገኖች ካቀረቡት ክስና መልስ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ተከራካሪ ወገኖችን ሲመረምር ከሚያገኘው መልስ ወይም ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች ካቀረቧቸው

[12] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223(1(ሀ) ምስክሮች የሚጠሩበት ዓላማ መገለጽ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

[13] Takwani, *supra* note 7, at 182.

[14] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 247/1፡፡

[15] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246/1፡፡

[16] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 247/2፡፡

ማስረጃዎች ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ትኩረት በሆነው ክስ መስማት ላይ ተወስነን በዚህ ደረጃ የምርመራ ውጤቶቹን ስንመለከት ሶስት መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ እነሱም፡- በአንዱ ወገን የተጠየቀው በሌላኛው ከተካደ ጭብጥ ይመሰረታል፣ ወይም በከፊል ከታመነ ከፊል ፍርድ ይሰጣል[17] ወይም የሚለያቸው ነገር ከሌለ በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ፍርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡[18]

የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ከዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ጋር በተያያዘ በአንድ ጉዳይ ያጋጠመውን ማንሳት እነዚህን ውጤቶች ለማየት ይረዳል፡፡ በአንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ሠራተኛውን በሰራው ጥፋት ከማገድ ውጭ አለማሰናበቱን ገልጾ ሠራተኛው ተመልሶ ስራውን ቢቀጥል ፈቃደኛ መሆኑን በመልሱም በቃል ክርክርም ወቅት አረጋገጠ፡፡ ሠራተኛው ደግሞ ተሰናብቻለሁ ሲል ተከራከረ፡፡ የተጠየቀው ዳኝነት ግን ወደ ሥራ መመለስ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ሠራተኛው ወደ ሥራ መመለሱ ላይ ክርክር ስለሌለ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ውሳኔ መስጠት ይችል ነበር፡፡ ቢያንስ ተፈፅሟል የተባለውን የሥራ ስንብት ወይም ከስራ የመታገድ ውጤት መመርመር ካለበት ሠራተኛው ሥራውን እየሰራ ውሳኔ ሊሰጥበት ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ ይዞ በጉዳዩ ላይ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ስንብቱ ሕጋዊ ነው የሚል ውሳኔ ከወራት በኋላ ሰጠ፡፡ አስፈላጊ ከነበረ ይህን ያህል ጊዜ ሳይወስድ እና ሠራተኛው ከሥራው ሳይፈናቀል ወይም ሳይስተጓጎል ክርክሩን ማካሄድ ይቻል ነበር፡፡ ከዚህ ጉዳይ መረዳት የሚቻለው የክስ መስማት ሂደቱ ሕጉ ባሰበው መንገድ ጥቅም ላይ ስላልዋለ እና ፍርድ ቤቱ በአግባቡ ጭብጥ ስላልያዘ ጊዜ ከመባከኑ በተጨማሪ አግባብ ያልሆነ ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክርክሩ አመራር ሥርዓትና አግባብ ተከትሎ ካልተካሄደ ፍትሐዊ ውሳኔ ላይ መድረስ እንደማይቻል በተለይም አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይመሰረት የሚሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው ሊባል የማይችል መሆኑን አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡[19] ከጭብጥ መያዝ በፊት ያለው ሂደት የክርክሩን ይዘት እና ለጭብጥ አያያዝ የሚረዱ ግብዓቶች የሚሰበሰቡበት ሲሆን በቀጣይ ያለው ሂደት ደግሞ ደጋፊ ማስረጃ በመቀበል በጭብጥነት ለተያዙት ጥያቄዎች መልስ ወይም ብያኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ ስለዚህ ጭብጡን ለመመስረት ተገቢው ግብዓት እንዲኖር እንዲሁም ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ትክክለኛውን ጭብጥ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ የተሳሳተ ጭብጥ መያዝ የተሳሳተ ውሳኔ ላይ ያደርሳል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ክስ መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔ ሊሰጥ መቻሉ አለመቻሉ ሊታሰብበት የሚገባ ነው፡፡ የክስ መስማት አስፈላጊነት የልዩነት ነጥብን አንጥሮ ማውጣት ነው ካልን ይህ ደግሞ በአንድ ጉዳይ ወይም ነጥብ ላይ የተለያየ አቋም የያዙ ተከራካሪዎችን ታሳቢ ያደርጋል፡፡ ሁሉም የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች የግድ በግራቀኝ የሚቆሙ ተከራካሪ ወገኖች (opponents) ስለማይኖራቸውና በዚህ ሁኔታ የልዩነት ነጥብ ስለማይኖር ከዓላማው አንጻር ክስ መስማት የማያስፈልገው ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ጉዳይ አለ ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ፍርድ ክርክርን ታሳቢ የሚያደርግ

[17] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 242፡፡

[18] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 254/1፡፡

[19] *የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ሞላ*፤ <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች</u>፣ ቅጽ 8፣ መዝገብ ቁጥር 37391 (2001)፡፡

ቢሆንም ተከራካሪ ወገን ሳይኖር ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በዚህ ውስጥ የሚታዩት ስምምነት ማጽደቅ (consent judgment)፣ አንደኛው ወገን በሌለበት ውሳኔ ሲሰጥ (ex-party/dafault judgment) እና በአጭር ሁኔታ ታይቶ የሚወሰን (summary judgment) ይገኙበታል፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ክስ መስማት አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 72 መንፈስ መረዳት የሚቻለው ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ባይኖርም የክስ መስማት ሂደቱ የሚቀጥል መሆኑን ሲሆን በዋናነት ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ጥያቄ ትክክለኛነት የሚያጣራ ስለሚሆንና ይህም የክስ መስማት ዓላማን የሚያሳካ በመሆኑ የሚያስከትለው ጉድለት የለም፡፡

## 4. ክስ መስማትን የሚያሳልጡ መርሆዎች

የመሰማት መብት ከአንድ ሀገር የሕግ አውጭ አካል ፍላጎትም በላይ የተፈጥሮ ፍትህ መርህ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑ በዚህ ፅሁፍ ክፍል 1 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ መርህ በራሱ ምሉዕ ቢሆንም አተገባበሩን የሚያግዙ ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች መርሆዎች አሉ፡፡ ተከራካሪ ወገኖችን ከመጥራት ጀምሮ በሂደቱ እንዲኖራቸው የሚደረገው ተሳትፎ እና በአጠቃላይ ሂደቱ በተገቢው ሁኔታ መከናወኑ ለመብቱ መከበር እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የመጥሪያ አደራረስ፣ በግልጽ ችሎት ማስቻል፣ ገለልተኝነት እና እኩልነት የመሳሰሉ መርሆዎች መከበር የመሰማት መብትን ውጤታማ ያደርጋሉ፡፡ ይህንን ለማሳየት ከዚህ በታች ስለነዚሁ ጉዳዮች መጠነኛ ዳሰሳ ይደረጋል፡፡

### 4.1. መጥሪያ

አንድ ሰው ክስ እንደቀረበበት ተረድቶ ክርክሩን ለማቅረብ የሚችለው በመጀመሪያ ክስ እንደቀረበበት እና የቀረበበትን ክስ ዝርዝር እንዲሁም መልስ ለመስጠት ወይም ክሱን ለመስማት የተያዘውን ቀጠሮ ሲያውቅ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ጉዳዩ ሲጀመር ብቻ ሳይሆን አንድ ጉዳይ ተቋርጦ ቆይቶ በአንደኛው ተከራካሪ ወገን አመልካችነት ሲንቀሳቀስ ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን መጠራትም ጋር ተያይዞ ይነሳል፡፡[20] ከመጥሪያ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ በአግባቡ ጥሪ ያልደረሰው ተከራካሪ ወገን የሚደርስበት ጉዳት የመሰማት መብት መገፈፍ መሆኑን ማስመር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ያለበቂ ጥሪት ሊታለፍ የማይችል መሠረታዊ መብት ስለሆነ መጥሪያ በአግባቡ ባልደረሰበት ሁኔታ በፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ውሳኔ ጥያቄ ላይ የሚጥል ነው፡፡ ስለዚህ የመጠራት ዓላማ የመሰማት ዕድልን ለመስጠት በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚሰጥ ትዕዛዝ ይህን መሠረታዊ መብት እንዳይገፍ ወይም እንዳያሳጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

ሕጉ መጥሪያ መድረስን ተከትሎ የአለመቅረብን ውጤት ሲያስቀምጥ ትኩረት የሰጠው ለክስ መስማት ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ ክሱን የመሰረዝ ውጤት ወይም በሌለበት እንዲታይ አቋም ለመያዝ መሠረት የሚያደርገው በመልስ መስጠት ሳይሆን በክስ መስማት ቀጠሮ አለመገኘትን ነው፡፡ መጥሪያ በዋናነት በክስ መስማት መገኘትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ሕጉ በዚህ ረገድ የሰጠውን ውጤት በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡ ከሳሹ

[20] እነ አቶ ታከለ አርዓያ እና አቶ ደጀን ገብረእግዚአብሔር፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ቅጽ 19 መ/ቁ. 107838፤ በ19/4/2008 የተወሰነ፡፡ መዝገብ ሲንቀሳቀስ ለተከሳሽ በተገቢው መንገድ መጥሪያ ሳይደርስ ውሳኔ መስጠት ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም የሚል አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ወይም ተከሳሹ በክስ መስማት ወቅት ባይቀርብ በቅደም ተከተል ክሱ እንዲሰረዝ ወይም በአግባቡ መጥሪያ መድረሱ ሲረጋገጥ ተከሳሹ በሌለበት እንዲታይ ሊታዘዝ ይችላል፡፡[21]

መጥሪያ መድረሱ አንድ ነገር ሆኖ የመሰማት መብት መተግበርን ለማረጋገጥ መጥሪያ ከቀጠሮው ቀን በፊት ምን ያህል ቀድሞ መሰጠቱና መጥሪያ ለሚደርሰው ተከሳሽ ወይም ባለጉዳይ ለመዘጋጀት የተሰጠው ጊዜ ከግምት መግባት አለበት፡፡ ይህ በዋናነት መልስ ከመስጠት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ሕጉ አለመቅረብን ውጤት የሚሰጠው ከክስ መስማት ጋር በተያያዘ ስለሆነ ከዚህ አንጻርም ሊታይ ይገባል፡፡ በተለይ መጥሪያ መልስ ለመስጠትና ክስ ለመስማት የሚሰጠው ጊዜ የተቀራረበ ሲሆን (ለምሳሌ ሁለት ቀናት) በዚህ ጽሑፍ ከተነሳው ጉዳይ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ ለመሰማት የቀጠሮውን መኖር ማወቅ አስፈላጊ ሲሆን ይህም በቂ ጊዜ በመስጠት የመብት አጠቃቀሙን ትርጉም ያለው ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በተለምዶ መጥሪያ ከአስር ቀን በፊት መድረስ አለበት[22] የሚል ግንዛቤ ያለ ቢሆንም ይህ ግንዛቤ የሕግ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ ለሁሉም ጉዳይ ተመሳሳይ ዝግጅት ከአለመጠየቁ ጋር ተዳምሮ ሲታይ ፍርድ ቤቶች የመጥሪያውን ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ የሚወስኑት መሆን አለበት፡፡[23] ዞሮ ዞሮ ግን የመሰማት መብት ተከበረ ሊባል የሚችለው አንድ ተከራካሪው ወገን ለዝግጅት የሚያስፈልገው በቂ ጊዜ ሲሰጠው ስለሆነ መጥሪያ የሚደርስበት ጊዜ ወይም በፍርድ ቤት የሚፈቀደው ጊዜ ይህንን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

### 4.2. በጠበቃ የመወከል መብት

ክስ መስማት የሚካሄደው ተከራካሪ ወገኖች በሕግ ወይም በፍሬ ነገር ረገድ ያላቸውን ክርክር ለመስማትና ጭብጡን ለመለየት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉንና አግባብ ያለውን ፍሬ ነገር ከሕግ አኳያ የሚኖረውን ውጤት ተረድቶ ክርክርን ለማቅረብ ሙያዊ እገዛ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ነው ያለጠበቃ እገዛ ይህ መብት ውጤታማ አይሆንም የሚል ክርክር የሚቀርበው፡፡ በአንድ ሕግ ውስጥ የሚገኙ ክስ መስማትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በሁሉም ረገድ ጥሩ ቢሆኑም በተለይም የተከራከሪ ወገኖችን እኩልነት (substantive and procedural equality) የሚያረጋግጡ ቢሆንም ተከራከሪ ወገኖች እኩል ሆነዋል (principle of equality of arms) ማለት አይደለም፡፡ በፍርድ ቤት ከሚያገለግሉ የቴክኒክ ቃላት ጀምሮ ሕጉንም አውቆና ፍሬ ነገሮች ከሕግ አንጻር የሚኖራቸውን ውጤት ተረድቶ ክርክርን ማካሄድ መስኩ የሚጠይቀውን ተገቢ እውቀትና ክህሎት መኖርን ይጠይቃል፡፡ ምንም እንኳ ሕጉ በጠበቃ መወከልን የሚፈቅድ ቢሆንም የተከራካሪ ወገኑ አቅም ካልፈቀደ መብቱ መከበሩ በራሱ የሚፈይደው ነገር የለም፡፡ በክስ መስማት ወቅትም በጠበቃ ያልተወከሉ ተከራካሪዎች

[21] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70(ሀ) እና 73፡፡

[22] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 240(2) ማስረጃ እንዲቀርብ ሲታዘዝ ትእዛዙ ለመስማት ከተያዘው ጊዜ ከአስር ቀን በፊት መድረስ እንዳለበት ተገልጧል፡፡

[23] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሐ/ መሠረት ተከሳሹ መጥሪያ የደረሰው መሆኑ ቢረጋገጥም ለተከሳሹ የተሰጠው ቀን ለክሱ መልስ ለማዘጋጀት በቂ ሆኖ በማይገመት አጭር ጊዜ መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው ሲሆን የክርክሩን መስማት ለሌላ ጊዜ እንደሚያስተላልፍ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ የተሰጠው ጊዜ በቂ ነው አይደለም የሚለው እንደነገሩ ሁኔታ በፍርድ ቤቱ የሚወሰን መሆኑን ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 192(1) እና 197(10) ይመለከቷል፡፡

በድንገት ለሚነሱ ጥያቄዎች ፍሬ ነገሩን፣ ሕጉንና ሁለቱ የሚኖራቸው መስተጋብርና ውጤት ተረድተው ተገቢውን ክርክር ለማድረግ መቻላቸው አጠራጣሪ ነው፡፡

ከዚህም በላይ ሕጉ የጠበቃን አስፈላጊነት የሚገባውን ቦታ ሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ በፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 197(3) የተከራካሪ ወገኖች ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ባለመቅረቡ ወይም መቅረብ ባለመቻሉ ምክንያት ቀጠሮ እንደማይቀየር ይደነግጋል፡፡ ይህም በፍርድ ቤቶች የጠበቆች መገኘት አለመቻል ሲገለጽ በዳኞች ተደጋግሞ የሚጠቀስ ድንጋጌ ነው፡፡ ሕጉ ጠበቃው የቀረበት ምክንያት ምንም ቢሆን የጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ አለመቅረብ ተቀባይነት እንደሌለው አድርጎ የወሰደ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ የሚኖር ክልከላ ወይም ፈቃድ በዋናነት ታሳቢ ማድረግ ያለበት የተከራካሪውን ወገን የመሰማት መብት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ጠበቃ ብቻውን እንዲሰራ በሚጠበቅበት ሥርዓት ውስጥ በግል ከሚደርስ እክል በተጨማሪ በድንገት ከፍርድ ቤቶች የሚላኩ መጥሪያዎች የጠበቃውን የጊዜ ሰሌዳ (አጀንዳ) ስለሚያዛቡ እና የሚተካው ባለሙያም ማግኘት ካልተቻለ የጠበቃውም ችግር ከግምት መግባት አለበት፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብት እና ለዚህ መብት ተግባራዊነት በጠበቃ የመወከል መብታቸው በተገቢው ሁኔታ ቦታ ካልተሰጠው የመሰማት መብት ተረጋግጧል ሊባል አይችልም፡፡

### 4.3. ግልጽ ችሎት

በዝግ የሚካሄድ የክርክር ሥርዓት ሁል ጊዜ አጠራጣሪ ነው፡፡[24] ሚዛንና ሰይፍ የተሰጠው ተሿሚ ዳኛ ሚዛኑንም ሆነ ሰይፉን በአግባቡ እንደሚጠቀምበት የሚረጋገጠው በአደባባይ በግልጽ ሥራ ላይ ሲያውለው ነው፡፡ አንድ አንድ ጊዜ እንደሚስተዋልው ዳኞች በጽህፈት ቤት የሚያሳዩትን ያልተገባ ባህሪ ተመልካች ባለበት ግልጽ ችሎት አይደግሙትም፡፡ ስለዚህ ከዚህ የበለጠ ግምት የሚሰጠው የተለየ መብት ከሌለ በስተቀር የመሰማት መብትም ተጠበቀ የምንለው ክርክሩ በግልጽ ችሎት ሲደረግ ነው፡፡ ይህ መብት በወንጀል አድራጊነት ከተከሰሱ ሰዎች አንጻር በኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 20(1) ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ ይህንኑ በአንድ ሰው መብት ወይም ግዴታ ላይ በፍትሐ ብሔር ችሎት ውሳኔ ሲሰጥ መጠበቅ አለበት በሚል ማስፋት ይቻላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁ. 25/1988 አንቀጽ 26 ለህዝብና መንግሥት ሰላምና ጸጥታ ወይም ለሕዝብ መልካም ጸባይ ወይም ግብረገብነት ሲባል ካልሆነ በስተቀር ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንደሚያስችሉ በግልጽ ደንግጓል፡፡ አገሪቱ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር ስናየው የዜጎችን በግልጽ ችሎት የመሰማት መብት የማረጋገጥ የመንግስት ግዴታ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በተለይ በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ መሰማት በግልጽ ችሎት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መጠቀሱን ስናይ ለመሰማት መብት ውጤታማነት በግልጽ ችሎት የማስቻልን አስፈላጊነት መረዳት አያዳግትም፡፡[25] ሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶችም ተመሳሳይ ይዘት እንዳላቸው ስናይ ይህ መብት የተሰጠውን ከፍተኛ ቦታ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የመሰማት ዕድል መሰጠቱ ብቻ ሳይሆን በግልጽ ችሎት መከናወኑ አጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

[24] That is why it is said that justice behind closed doors will soon reek to high heaven.

[25] Universal Declaration of Human Rights, 1948, Art 10.

## 4.4. የተከራካሪ ወገኖች እኩልነትና የዳኞች ገለልተኝነት

ፍርድ ቤቶች ገለልተኛ እንዲሆኑ ያለባቸው ግዴታ ተቀጽላ ሆኖ ክስ ሲሰማ ዳኞች የተጣለባቸው የገለልተኝነት ግዴታ እንደተጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ፍርድ ቤቶች ከውሳኔ ሊደርሱ የሚገባው የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት፣ የመከላከል ብሎም በእኩልነት መርህ የመዳኘት መብት በጠበቀ መልኩ መሆን ያለበት ሲሆን ‹‹አግባብነት ባለው መንገድ ሳያጣሩ/ሳያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም›› መሆኑ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡[26] በሕግ እና በሥነ-ሥርዓት ረገድ በተከራካሪ ወገኖች መካከል እኩልነት (substantive and procedural equality) መኖር ሲሆን የተከራካሪዎች እኩልነት በክስ መስማት ወቅትም መጠበቅ እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡

እኩልነት ተረጋገጠ የሚባለው ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች እኩል ዕድል ሲሰጡ ነው፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት የዳኛ ገለልተኛ መሆን ማሳያው ምን መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ከክስ መስማት ዓላማ አንጻር በዚህ ሂደት የሚጠበቀው የሚያለያይ ነገር መኖሩን ማረጋገጥና አከራካሪ ነጥብ ካለ ይህንኑ መለየት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የእኩልነት መብት ተጠበቀ የሚባለው ምን ሲሟላ ነው የሚለው ጥያቄ ቀላል መልስ አይገኝለትም፡፡ በተለይ በዚህ ደረጃ ጉዳዩን የማጣራት ሥራ የሚሰራበት ሂደት በመሆኑ በዋናነት ጥያቄውን የሚያቀርበው ፍርድ ቤቱ በመሆኑና ፍርድ ቤቱ መጠየቅ ያለበት ማብራሪያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዩች ላይ ብቻ በመሆኑ ለሁለቱም ወገን እኩል እድል መስጠት አይጠበቅበትም፡፡ ስለዚህ በዋናነት የዳኞች ሥራ የሚሆነው ተገቢው ጥያቄ ለተከራካሪ ወገኖች በማቅረብ የልዩነት ነጥቡን ማጥራት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ዳኞች አስፈላጊውን እና ተገቢውን ጥያቄ ለሚመለከተው ተከራካሪ ወገን በማቅረብ ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ከመጣር ውጭ ለሁለቱም ወገን እኩል የመናገር እድል መስጠት አይጠበቅባቸውም፡፡ ይህን በማድረጋቸውም እኩል የመስተናገድ ጥያቄ ሊነሳም ሆነ በተነሳው ነጥብ ላይ ሁሉ የመናገር ዕድል ሌላኛው ወገን የሚጠይቅበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡

በእርግጥ በዳኞች በኩል ይህን መርህ ለማስጠበቅ የሚደረገው ጥረት በእነርሱ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም፡፡ በችሎቶች በተደጋጋሚ እንደሚስተዋለው ሁለቱም ወገኖች በጠበቃ ባልተወከሉበት ሁኔታ ዳኞች ፈተና ሲገጥማቸው ይታያል፡፡ በዚህ ሁኔታ በጠበቃ ያልተወከለው ተከራካሪ የሕግ ቃላትን ትርጉም አለመረዳት፣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ቃል የሚኖረውን ውጤት ያለመገንዘብ ችግር እንዲሁም ተገቢውን ባለማድረግ የመብት መጣበብ የሚከሰትበት አጋጣሚ አለ፡፡ እኩል አቅም ሳይኖር እኩል እድል ቢሰጥ የእኩልነት መብት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ ዳኞች የሚከተለውን ኢፍትሐዊ ውጤት በመገመት በባለሙያ ያልተወከለውን ወገን ለመርዳት የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ይህም ገለልተኝነታቸው ላይ ወይም ስለ እኩልነት መብት ጥያቄ ያስነሳል፡፡

[26] እነ አቶ በቀለ አማረ /ሁለት ሰዎች/ እና ወ/ሮ ብዙነሽ ግርማ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ ቅጽ 12 መ/ቁ. 52546 በ3/4/2003 የተወሰነ፡፡

## 5. ክስ የመስማት ሂደት

አንድ ጉዳይ የሚጀመረው በከሳሽ በሚቀርበው ክስ ሲሆን ይህን ተከትሎ በተከሳሽ መልስ ይሰጣል፡፡ እነዚህን ሁለት የክርክር ደረጃዎች ተከትሎ የሚመጣው ሶስተኛው ደረጃ ክስ መስማት ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የክርክር ሂደቶች በጽሑፍ የሚከናወኑ ሲሆን ሶስተኛው ግን ፍርድ ቤቱ አከራካሪውን ነጥብ ለመለየት የሚጠቀምበት በቃል የሚደረግ ጥያቄ እና መልስ ነው፡፡ በዚህ ፅሁፍ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይኸን ሂደት በተመለከተ የስያሜ መምታታት ስላለ ለማየት የሚሞከረው ክስ መስማትን (hearing) እንጂ ክርክር መስማትን (trial) ባለመሆኑ በዚህ ንዑስ-ርዕስ የሚደረገው ገለፃ በዚሁ የተወሰነ ይሆናል፡፡

በዕለት ተዕለት የባለሙያዎች የቃላት አጠቃቀም መገንዘብ የሚቻለው ክስ መስማት ከመልስ መቅረብ በኋላ ባለ ቀጠሮ የሚከናወን ሥራ ተደርጎ እንደሚወሰድ ነው፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደቀረበው ክስ መስማት የአንድ ቀን ክንውን ሳይሆን መጀመሪያውና መጨረሻው በተለያዩ ቀናት ሊሆን የሚችል ተከታታይነት ያለው ሂደት ሊሆን እንደሚችል ከሕጉ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ የሆነ ሆኖ ክስ መስማት የሚጀመረው ተከራካሪዎችን በመመርመር መሆኑን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241(1) ድንጋጌ ይገልጻል፡፡ ፍርድ ቤቱም ወደ ጉዳዩ ይዘት ከመሄዱ በፊት የተከራካሪ ወገኖችን ወይም ወኪሎችን ማንነት መለየት አለበት፡፡ ከተሞክሮ መናገር የሚቻለው በክስ መስማት ወቅት የቀረቡትን ተከራካሪዎች መለየት ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ይህም በክስ መክፈት እና በመልስ መስጠት ወቅት በተደረገው ማጣራት ላይ በመተማመን ይመስላል፡፡ ነገር ግን በሕጉ ላይ ማሻሻያ እስካልተደረገ ድረስ ሥርዓቱ መፈጸም ያለበት ከመሆኑም በላይ ከላይ የቀረበው ምክንያት ልክም ቢሆን የቀረበው ሰው በክሱ ስሙ የተጠቀሰው ተከራካሪ ወይም ወኪሉ ስለመሆኑ ማጣራትን የሚያስቀር አይደለም፡፡ ከዚህም በላይ በዚህ ዕለት በሚሰጥ የእምነት ቃል ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል በመሆኑ የእምነት ቃሉን የሚሰጠው ሰው ስሙ የተጠቀሰው ወይም ቢፈረድበት ፍርዱን የሚፈጽመው ሰው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ሂደቱን ስናይ ክስ መስማት የሚጀመረው የተከራካሪዎቹ ማንነት ከተለየ በኋላ የቀረበውን ክስና የተሰጠውን መልስ በማንበብ እንደሆነ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241(1) ይገልጻል፡፡ ይህ ሂደት ሙሉበሙሉ በዳኛ የሚመራ ነው፡፡ ክስ እና መልስ እንደሚነበብ በህጉ የተቀመጠ ቢሆንም በተግባር ግን ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር የተጠጋጋ ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው ተግባር አንዳንድ ዳኞች ክሱን በአጭሩ የሚገልጹ መሆኑ ነው፡፡ በአመዛኙ ግን ዳኛው እንደሚከተለው የክስ መስማት ዘይቤ በቀጥታ ወደ ማጣራት መሄዱ የተለመደ ነው፡፡ እዚህ ላይ የክስ ማንበብ አስፈላጊነት ጥያቄ ሊነሳበት የሚገባ በተግባርም ብዙም የማይፈጸም መሆኑና እስከ አሁንም የጎላ ችግር አለመከሰቱ ሲታይ ሕጉን በማሻሻል ዳኞችን ከዚህ የስራ ጫና ነጻ ማድረጉ ለክስ መስማት የሚመደበውንም ጊዜ መቀነሱ የተሻለ ሊመስል ይችላል፡፡ በእርግጥ ለሌላኛው ተከራካሪ ወገን የሚደርሰውና ለፍርድ ቤቱ የሚቀርበው ማመልከቻ ይዘት ሊለያይ የመቻሉ እድል ሙሉ በሙሉ የለም ማለት በማይቻልበት ሁኔታ ማመልከቻዎቹ መነበባቸው አስፈላጊ መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ በሥራ ላይ ባለው የፍሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መነበቡ የግድ ስለሆነ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተከትለው መስራታቸው የግድ ነው፡፡

*የአቤቱታ ማመልከቻዎቹ መነበብን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ተከራካሪ ወገኖችን ይመረምራል፡፡ በዚህ መሠረት የሚሰጥ የእምነት ወይም ክህደት ቃል ተመዝግቦ የመዝገቡ አካል ይሆናል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሠረት ተከራካሪዎቹ ለዳኛው ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ዳኛው ጽፎ እንደሚመዘግበው ሲሆን አሁን በከፍተኛው ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ ባለው አሰራር ፍርድ ቤቶች ክርክርን በመቅረፀ-ድምፅ አስቀርተው በጽሑፍ በመገልበጥ የመዝገቡ አካል የሚያደርጉበት አሰራር እየተዘረጋ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ክስ መስማት በጽሑፍ ሰፍሮ ወይም በመቅረፀ-ድምፅ ተቀርጾ ከሆነ ደግሞ ወደ ጽሑፍ ተቀይሮ የመዝገቡ አካል መሆን አለበት፡፡ የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ እንደታዘበው ጉዳዮች በይግባኝ በበላይ ፍርድ ቤቶች በሚሰሙበት ወቅት በበርካታ አጋጣሚዎች ከሚሰሙት ቅሬታዎች መካከል በቃል ክርክር ወቅት ያላልኩት ተመዝግቧል የሚለው ነው፡፡ በመቅረፀ-ድምፅ የተያዘው ከቴክኒክ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ከሚነሳው ቅሬታ በቀር ብዙም ክርክር ሲያስነሳ አይታይም፡፡ በጽሑፍ የሚያዘው ግን ሙሉበሙሉ በእምነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሬት ላይ ያለው እውነታ እንደሚያረጋግጠው በፍርድ ሂደት በማንኛውም የአሠራር ሥርዓት በየትኛውም ደረጃ የሰውን ተሳትፎ ለመቀነስ ቢሞከርም ማስቀረት ግን አይቻልም፡፡ ስለዚህ የሰው ተሳትፎ ማስፈለጉ ስለማይቀር ዋናው ነጥብ የሚሆነው እምነት የሚጣልበት ሰው መሾም እና ሲሳሳትም ማረም የሚችል ሥርዓት መዘርጋት ላይ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ከሚሰጣቸው ስልጣንና ካለባቸው ኃላፊነት አንጻር የዳኞች ታማኝ መሆን በምንም የማይተካ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ካልሆነ ግን ተከራካሪ ወገኖች ያላሉት ተመዝግቦ ሊገኝ የሚችልበት ሁኔታ በፍጹም አይከሰትም የሚባል አይደለም፡፡*

*የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በቀረበበት ሁኔታ የክርክሩ ሂደት የተለየ መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡ ለቀረበ መቃወሚያ እልባት የሚሰጠው ከክርክር መስማት በፊት በክስ መስማት ጊዜ ነው፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ክስ ከተነበበ በኋላ በፍርድ ቤት የሚደረገው ማጣራት መቃወሚያው ላይ መወሰን አለበት ወይስ ወደ ዋናው ጉዳይ ይገባል የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በአሰራር ሁለት ዓይነት አካሄዶች አሉ፡፡ አንደኛው ሙሉውን ጉዳይ መስማት ሲሆን ሁለተኛው ግን መቃወሚያው ላይ ብቻ ማጣራት አድርጎ ብይን ከተሰጠ በኋላ ጉዳዩ ከቀጠለ በዋናው ጉዳይ ላይ ክስ የሚሰማበት አካሄድ ነው፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244(1) ድንጋጌ መረዳት የሚቻለው ለመቃወሚያ እልባት የሚሰጠው ከክርክር መስማት በፊት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ክስ መስማት ተጠናቆ ወደ ክርክር መስማት ከመኬዱ በፊት በመቃወሚያ ላይ ውሳኔ የሚሰጥ በመሆኑ ክስ መስማቱ መቃወሚያውንም ሆነ ዋናውን ጉዳይ የሚሸፍን ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246(1) ጭብጥ የሚያዘው በመቃወሚያ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በዋናው ጉዳይ ላይ ክስ መስማት በመቃወሚው ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ እንደሚቀጥል ምንም ፍንጭ አይሰጥም፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ክስ መስማቱ በተሟላ ሁኔታ ከተደረገ በኋላ ጭብጥ ከመያዙና ወደ ክርክር መስማት ከመኬዱ በፊት በመቃወሚያ ላይ ብይን የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡*

*ሆኖም ግን የፍርድ ቤት ጊዜን በአግባቡ ከመጠቀም አንጻር ተገቢነቱ ላይ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ወደ ፊት አገልግሎት ሊሰጥ ያለመቻሉ ዕድል መኖሩ እየታወቀ የዳኞች፣ የተከራካሪ ወገኖች፣ የረዳት ሰራተኞች ጊዜና ጉልበት የሚባክንበት ምክንያት ሊኖር*

አይገባም፡፡ በተለይም ጉዳዩ ውስብስብ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ለክስ መስማት የሚመድቡት ጊዜ ብዙ ስለሚሆንና ይህም ትርጉም የለሽ መሆኑ ሲታይ ሂደቱን በሁለት መክፈል የተሻለ ነው፡፡ የክስ መስማት ተከታታይነት ያለው የማጣራት ስራ የሚሰራበት ሂደት ከመሆኑ አንጻር በዚህ መልክ ተከፋፍሎ የማጣራቱ ስራ ቢሰራ በማዕቀፉ ውስጥ የሚወድቅ ይሆናል፡፡

መቃወሚያው የክርክሩን ማብቃት የማያስከትል ከሆነ ቀጣዩ ክንውን ጭብጥ መመስረት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ጉዳዩች ጭብጥ መመስረት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ በመጀመሪያ አከራካሪ ነገር ከሌለ ወይም ክሱ ከታመነ ጉዳዩ በፍርድ ያበቃል፡፡ ፍርዱ ጉዳዩን በከፊል ወይም በሙሉ የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ መፍትሔ ያላገኘ ጉዳይ ጭብጥ መያዝን የግድ ላያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ተከሳሽ ነገሩ በመጀመሪያ በሚሰማበት ቀን ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ እንዲይዝ አይገደድም፡፡[27] አከራካሪ ነገር ከሌለ[28] ወይም የቀረበው ክስ ከታመነ[29] ጭብጥ ሳይመሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡[30] ክሱ ሙሉ በሙሉ ከታመነ የመጀመሪያው ቀጠሮ የመጨረሻውም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በዚህ ደረጃ በከፊል ወይም ሙሉበሙሉ እልባት ባላገኘ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ የመለየት ሥራ መስራት አለበት፡፡

ጭብጡ የሚመሠረተው በሚከናወነው የማጣራት ሥራ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ክስና መልሳቸውን ከአቀረቡ በኋላ የማጣራት ወይም የመመርመር ሥራው የሚመራው በፍርድ ቤቱ ነው፡፡ የክስ መስማቱ የሚከናወነው በፍርድ ቤቱ ዳኛ ወይም ዳኞች ሲሆን ቁጥራቸው ምንም ቢሆን የተከራካሪ ወገኖች ምላሽ የሚመዘገበው በአንዱ ዳኛ ነው፡፡ ሶስት ወይም ከዛ በላይ ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎቶች ክሱ መሰማት ያለበት በተሟላ ችሎት ነው፡፡[31] የተከራካሪዎች ምርመራ በዋናነት ዳኞች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የሚመራ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የጎንዮሽ መስተጋብር ስለማይኖራቸው ቀጥታ ምልልስ ለማድረግ አይችሉም፡፡ በአሰራር ብዙም ያልተለመደው ተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለሌላው የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡ ሕጉ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ ለሌላው ጥያቄ ካለው ፍርድ ቤቱ እንዲጠይቅለት ማመልከት ይችላል ሲል ይደነግጋል፡፡[32] ስለዚህ በጥያቄ ሂደት ጠያቂው ፍርድ ቤት ብቻ ቢሆንም ከተከራካሪዎች አንዱ ለሌላው የሚያነሳው ጥያቄ ካለ በፍርድ ቤት አማካኝነት መጠየቅ ይችላል፡፡

ከላይ እንደቀረበው የክስ መስማት ሂደት የሁለቱም ወገኖችን መቅረብ ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡ የተከራካሪ ወገኖች መቅረብ ፍርድ ቤቱ የሚያደርገውን ማጣራት ምሉእ

---

[27] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246(2)፡፡

[28] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 254(1)፡፡ በታመነ ነጥብ ላይ ክርክር እንደማይካሄድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ *ሳስኮ ኢንደስትሪል ንግድና ት/ት ድርጅት እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ት/ሚኒስቴር*፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ቅጽ 21 መ/ቁ. 124669፣ በ30/3/2009 ዓ. ም. የተወሰነ፡፡

[29] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 242፡፡ *የዳንግላ ወረዳ ውሃ ሐብት ልማት ጽ/ቤት እና እነ አቶ ሙሉጌታ ገበየሁ*፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ቅጽ 20 መ/ቁ. 107217፣ በ29/3/2009 ዓ. ም. የተወሰነ፡፡

[30] *የማርዘነብ እቁብ ዳኛ እና እነ አቶ ዋለልኝ ተመስገን*፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች፣ቅጽ 19 መ/ቁ. 112927፣ በ16/6/2008 ዓ. ም. የተወሰነ፡፡

[31] አዋጅ ቁ. 25/1988 አንቀጽ 20(2)፡፡

[32] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 142/2፡፡

የሚያደርገው ቢሆንም የአንደኛው መቅረት ሂደቱን ሊያስተጓጉል አይችልም፡፡ ለምሳሌ ከሳሽ ክስ ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ ባይቀርብ መዝገቡ ወዲያውኑ አይዘጋም፡፡ በመጀመሪያ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ስለማመን ወይም መካዱ ያረጋግጣል፡፡ በከፊል ወይም በሙሉ ከታመነ ፍርድ የሚሰጥ ሲሆን ከተካደ ግን መዝገቡን ይዘጋል፡፡[33] በሌላ በኩል በአግባቡ መጥሪያ የደረሰው ተከሳሽ አለመቅረብ ውጤት ጉዳዩ በሌለበት መሰማት ነው፡፡[34] ሆኖም ሁሉም ጉዳዮች በተቃራኒ የሚቆም ተከራካሪ ላይኖራቸው የሚችል መሆኑና ተቃራኒ ወገኖች ተስማምተው የሚቀርቡበት ሁኔታ ስላለ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ጭብጥ መያዝ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቱን ክስ መስማት ሳያስፈልገው ወደ ቀጣይ ሂደት እንዲያልፍ የሚያስችል ነው፡፡ ለምሳሌ የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ በተገኘበት አንድ የችሎት ውሎ በተስተናገደ አንድ ጉዳይ ስምምነታቸው እንዲጸድቅ በጋራ ያመለከቱ ተጋቢዎች ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ምንም የሚያከራክራቸው ጉዳይ እንደሌለ ሲያሳውቁ መከራከር እንዳለባቸውና ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ተጨማሪ ትዕዛዝ ተሰጣቸው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ከዚህ በታች ከተገለፀው የተዘበራረቀ አሰራር በተጨማሪ ክስ መስማት የክስ መስማትን ዓላማ በማያሳካ ሁኔታ የሚተገበርበት አጋጣሚ መኖሩን ነው፡፡

የክስ መስማት ሂደት ሲጠናቀቅ ቀጠሮ የሚሰጥ ሲሆን ቀጠሮ ሲሰጥ በጣም ተደጋግሞ ከጠበቆች የሚቀርብ ጥያቄ ለምን ዓላማ እንደተቀጠረ ለመረዳት ነው፡፡ ለዚህ አሁንም ድረስ ለሚቀርብ ጥያቄ በአብዛኛው የሚሰጠው ምላሽ ለምርመራ የሚል ነው፡፡ ነገር ግን በፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህጉ በተቀመጠው አካሄድ ዳኞች ምርመራ የሚያካሂዱት ተከራካሪ ወገኖችን ሰምተው ሳይሆን በጽሑፍ የቀረበውን አይተው መብራራት ያለበትን በጥያቄ እንዲነጥር በማድረግ ነው፡፡ ክስ ከተሰማ በኋላ ቀጣይ ስራ ጭብጡን መለየት ነው፤ ቀጥሎም የሚኖረው ሂደት ክርክር መስማት (trial) ነው፡፡ ይህም እስከ ክስ መስማት ድረስ ባለው ሂደት የተሰባሰቡ የጭብጥ ምንጮች ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ምንአልባት ጭብጡን ለመያዝ ተጨማሪ ሰነዶችን መመርመር ወይም ምስክሮችን መስማት ካስፈለገ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ከመያዙ በፊት ይህንኑ ማከናወን ይችላል፡፡[35] ይህም በፍርድ ቤቱ ወይም በተከራካሪዎች የጽሑፍ ስምምነት[36] የሚወሰን ነው፡፡ ስለዚህ የፍርድ ቤቱ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በጭብጥነት በተለዩ የሕግ እና/ወይም የፍሬ ነገር ጥያቄዎች ላይ ይሆናል፡፡ ቀጣይ ሂደቶችም እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚውሉ ሲሆን ይህም ወደ ክርክር መስማት ወይም ውሳኔ ሊያመራ ይችላል፡፡[37]

## 6. የክስ መስማት ዘይቤዎች

ሕጉ ክስ መስማት የሚለው የፍርድ ሂደት ደረጃ ምን ሥርዓቶችን እንደሚያካትት ከላይ ተገልጿል፡፡ አተገባበሩ ሲታይ ግን በሕጉ እንደተቀመጠው ወጥ አይደለም፡፡ የዚህ

[33] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73፡፡

[34] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70፡፡

[35] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 249፡፡

[36] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 252፡፡

[37] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 255፡፡

*ፅሁፍ አዘጋጅ ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ጊዜያት ያስተዋለውና ከሌሎችም የሙያ አጋሮች ጋር ካደረገው ውይይት እንደተረዳው አሁን ባለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሠራር መሠረት የሚከተሉት የክርክር አሰማም ዘይቤዎች ተለይተዋል፡፡*

1. *ተከራካሪ ወገኖች በጽሑፍ ያቀረቡትን ደግመው በንግግር እንዲያቀርቡ የሚጋበዙበት፤*
2. *ዳኛው አንብበው በመምጣት በአጭሩ ክሱንና መልሱን ካብራሩ በኂላ በአጭሩ እንዲናገሩ ለተከራካሪ ወገኖች እድል የሚሰጡበት፤*
3. *ዳኛው ጉዳዩን አጥንተው አከራካሪ ነጥቦችን በመለየት ጥያቄዎችን የሚጠይቁበት (ይህ በሁለት ይከፈላል፤ አንዳንዶቹ በተመሳሳይ ጥያቄ ላይ የሁለቱንም ሐሳብ የሚሰሙ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ለያንዳንዱ ተከራካሪ የተለያየ ጥያቄ ያቀርባሉ)፤*
4. *በአንደኛው ተከራካሪ ወገን በተነሳ ነጥብ ላይ ሌላኛውን ወገን አንተስ ምን ትላለህ በማለት ማብራሪያ የሚጠይቁበት፤*
5. *አንዳንድ ዳኞች በክሱ ወይም በመልሱ ውስጥ የተነሱ ነጥቦችን እያነሱ ከሚመለከተው ተከራካሪ ጋር ሙግት የሚገጥሙበት ነው፡፡*[38]

*ከዚህ መረዳት የሚቻለው ክስ መስማትን በተመለከተ ተመሳሳይ ግንዛቤም ሆነ አሰራር የሌለ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ደረጃ የሚከናወነው ያለፈውን ሰፊ መነሻ (በክስና በመልስ የሚነሱ ዝርዝር ክርክሮች) የሚጠቡበት እና የወደፊቱን ሂደት አቅጣጫ ለማስያዝ የሚረዳ ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እና ሂደቱ ተገማች ሊሆን ይገባል፡፡ የክስ መስማት የተነሱትን የህግና የፍሬ ነገር ነጥቦች ወደ አከራካሪ ነጥብ በማጥበብ እና ቀጣይ ሂደቱን በዚሁ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የፍርድ ቤትን፣ የተከራካሪዎችን እና የምስክሮችን ጊዜና የአገር ሀብት ለማዳን የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት በተግባር የሚታዩ የክስ መስማት ዘይቤዎች የሂደቱን ተገማችነት የሚጎዱ ከመሆኑም በላይ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት አያስችሉም፡፡ በእርግጥ በሕግ የተቀመጠው አሰራር መፈተሽ ያለበት መሆኑ አሌ ባይባልም ይህ ለውጥ እስኪመጣ ድረስ ሕጉን ጠብቆ ሂደቱን መምራት ያስፈልጋል፡፡*

*ከክስ መስማት በፊት ያለው ሂደት በተከራካሪ ወገኖች ቁጥጥር ሥር የሚቆይ ነው፡፡ በክሱ የሚዘረዘረውን እንዲሁም የሚቀርበውን ማስረጃ ከሳሹ የሚወስን ሲሆን መልሱም በተመሳሳይ ሁኔታ በተከሳሽ ይዘጋጃል፡፡ ክስ ሲቀርብ አልፎ አልፎም መልስ ሲቀርብ በአመዛኙ ከማመልከቻዎቹ ፎርም ጋር የተያያዘ ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን የጎደለ ቢኖር በሚሟላት የሚታለፍ ነው፡፡ ክስ መስማት ደረጃ ሲደረስ ግን ሂደቱ በዳኛው ሙሉ ቁጥጥር ስር የሚውልበት ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤቱ በሚደረግ ማጣራት ሲፈቀድላቸው ተሳታፊ ከመሆን ባለፈ ሂደቱን የመቆጣጠር ሚና ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ የሚያከራክራቸውን ነጥብና ከዚህ ጋር*

[38] እነዚህ ተደጋግመው የሚታዩ እንጂ ሌሎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ በተናጠል የሚገጥሙ ሁኔታዎች ዝርዝር በርካታ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ጉዳይ ክስ ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ ተከሳሹን ‹ተከሳሽ ስለሆንክ አትናገርም› ተብሎ የተከለከለበት አጋጣሚ አለ፡፡ በሌላ ጊዜ ከአንደኛው ተከራካሪ ንግግር ለቀም በማድረግ ወቀሳ በመጨመር ሌላኛውን ተከራከሪ መሞገት እና በዚህ ምልልስ ከግማሽ ሰዓት በላይ የፈጀ ክርክር በአንድ የሥራ ክርክር ጉዳይ ጸሐፊው ታዝቧል፡፡

ይዛመዳሉ ያሉዋቸውን ነገሮች ለይተው ስላቀረቡለት በፍሬ ነገር ወይም በሕግ ረገድ የሚጣራውን የመለየት ስራ የሚሰራው በራሱ በሚመራ ሥርዓት ነው፡፡ ባለጉዳዮች ‹ጀምር› ተብለው የፈለጉትን እንዲናገሩ ሊጋበዙ አይገባም፣ ‹ተናገር› ተብለው በነጻት የሚለቀቁበት አሰራር ሊኖር አይችልም፡፡ በሕግ ከተደነገገው በተጨማሪ ከጊዜም ሆነ ከሀብት አጠቃቀም አንጻር ተገቢ አይደለም፡፡ በዚህ ደረጃ ፍርድ ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን የይገባኛል ጥያቄና መከላከያ ምን እንደሆነ ለይቷል፡፡ ስለዚህ በጽሑፍ የቀረበው በድጋሚ በተከራከሪ ወገኖች በንባብም ሆነ በአጭሩ እንዲያቀርብ ማድረግ ተገቢ አይደለም፡፡

በፍርድ ቤቱ የሚቀርበውም ጥያቄ ለማብራራት የሚረዳ በመሆኑ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በአንድ ጉዳይ/ጥያቄ ላይ ግራ ቀኙ መናገር የለባቸውም፡፡ በዚህ ደረጃ የማጣራት፣ ምርት ከገለባ የመለየትና ትኩረት የሚደረግበትን ነቅሶ የማውጣት ግብ ስለተያዘ ለዚህ ዓላማ የሚጠቅም ጥያቄ ግልጽ ማድረግ ለሚጠበቅበት ተከራከሪ ወገን ከማቅረብ ማለፍ የለበትም፡፡ በሌላ በኩል ዳኛ ሐሳቡን የሚገልጸው በውሳኔ ስለሆነ ከውሳኔው በፊት አቋም ይዞ ሊሚገት የሚችልበት ሁኔታ መኖር የለበትም፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ተከራክሮ ለማሳመን የሚጥሩ ዳኞች መኖራቸው አልፎ አልፎ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ደረጃ ተከራካሪ ወገኖችን የሚለያያቸውን ነጥብ ከመለየት ያለፈ አቋም የሚያዝበት አይደለም፡፡ ክስ መስማት የክርክር መስማት ሂደቱ የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች በመለየት በማስረጃ እንዲነጥሩ የማድረግ ሥርዓት የሚከተል በመሆኑ አቋም ለመያዝ የሚያበቃ ሁኔታ የለም፡፡

ጭብጥ ለመለየት ግብዓት የሚሆኑት በተከራካሪ ወገኖች የቀረበው ክስ፣ መልስ፣ በተከራካሪ ወገኖች የቀረቡ የጽሑፍ ማስረጃዎች እና በክስ መስማት ወቅት በተከራካሪ ወገኖች የሚሰጥ መልስ ነው፡፡ ሁለቱ ምንጮች በተከራካሪ ወገኖች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ለመመስረት የሚኖረው በግብዓትነት አስተዋጽዎ የማድረግ ሚና በክስ መስማት ወቅት የተወሰነ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ከላይ እንደተገለፀው ፍርድ ቤቱ የሚመራው የጥያቄና መልስ ጊዜ ይኖራል፡፡ በዚህ ወቅት የሚሰጠው መልስ ለጭብጥ አመሰራረት ግብዓት እንደሚሆን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 248(ሐ) መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሠረት ክስ መስማት ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤቱ በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት ከሚሰጡት መልስ ውጭ በራሳቸው የሚያደርጉት ገለጻ ወይም የሚሰጡት ማብራሪያ የለም፡፡ ተከራካሪዎቹ ስለክስ ወይም መልስ እንዲያስረዱም መጋበዝ የለባቸውም፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በክስ ወይም መልስ ውስጥ ከገለጹት ውጭ (extraneous information) ሊከራከሩ ስለማይችሉ እና አስፈላጊ ከሆነም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ አመልካችነት ወይም በራሱ አነሳሽነት ፍርድ ቤቱ የክስ ወይም መልስ መሻሻል ማዘዝ የሚችል ከመሆኑ በስተቀር ክርክሩ በአቤቱታ ማመልከቻዎቹ ከተገለፀው ሊወጣ አይችልም፡፡[39] በክስ ወይም በመልስ የሚነሱት ክርክሮች ሰፊ ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ ፍሬውን ከገለባው መለየት አለበት፡፡ ይህን ፍርድ ቤቱ ለማድረግ በተከራካሪ ወገኖች ከተዘረዘረው ውስጥ ግራ ቀኙ የሚስማሙበት ነገሮች ላይ ጊዜ ሊያጠፋ አይገባም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕግ ትኩረት የሚሰጠው ለማንኛውም ፍሬ ነገር ሳይሆን ለጉዳዩ አግባነት ያለው ሲሆን ነው፡፡ አንድ ነገር

[39] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 90 እና 91፡፡ *አቶ ኪዳኔ ገብረጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን*፣ <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች</u>፣ ቅጽ 6 መ/ቁ. 31547 በ20/7/2000 የተወሰነ፡፡ የክርክ ጭብጥ ባልሆነ ነገር ላይ ተመስርቶ ጭብጥ መያዝ እንደማይቻል አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለጉዳዩ አግባብነት አለው የሚባለው ደግሞ የከሳሽ መብት ለመመስረት የሚያስችል ወይም የተከሳሹ መከላከያ ለመሆን የሚችል ማናቸውም በሕግ ወይም በማስረጃ የተደገፈ ፍሬ ነገር ነው፡፡[40] ስለዚህ በፍርድ ቤቱ ለተከራካሪ ወገኖች የሚቀርበው በተከራካሪ ወገኖችም ምላሽ የሚሰጠው አግባብነት ባለው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ መሆን አለበት፡፡

## ማጠቃለያ

የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ግቡን በግልፅ ባያስቀምጥም ተመሳሳይ ሕጎች ከሚኖራቸው ዓላማ  አንጻር አለመግባባቶች በገለልተኛ የዳኝነት ተቋም ሥነ-ሥርዓትና ፍትሐዊነት በጠበቀ ሁኔታ በፍጥነትና በአነስተኛ ወጪ መፈታታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ የክስ መስማት ሂደት እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት በሚያስችል መንገድ መከናወን አለበት፡፡ በሕግ ማሻሻል የሚፈቱ ችግሮች መኖራቸውን ሳንረሳ ባለው ሕግ አተገባበር ላይ የሚታዩ ችግሮችን በማስወገድ የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረበው አንጻር አሁን ያለው አሰራር ወጥነት ስለሌለው ተገማች ካለመሆኑም በላይ ፍጥነትንና ወጪ ቁጠባን ለማሳካት አይረዳም፡፡ የውጤቱ ጥራት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተጽእኖም በውሳኔዎች ላይ ሲንጸባረቅ ይታያል፡፡ የሆነ ሆኖ ሥርዓት ለማስጠበቅ የተዘጋጀው ሕግ በተዘበራረቀና ወጥነት በሌለው ሁኔታ ሥራ ላይ ሲውል በተወሰኑ የፍርድ ቤት ውሎዎች ማንም የሚታዘበው ነው፡፡ ይህ ለምን ሆነ የሚለው ተጨማሪ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም የተዘበራረቀ አሰራር መኖሩ ሲስተዋል በቶሎ አለመታረሙ እና ከትምህርት አሰጣጥ ጀምሮ የተዘበራረቀ ልምድ መኖር ለዚህ ሁኔታ መቀጠል አስተዋጽኦ ማድረጉን መረዳት ይቻላል፡፡

የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች አንዱ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቱ ተገማች እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ባለጉዳዮች የትኛውም ፍርድ ቤት ወይም ዳኛ ዘንድ ቢቀርቡ ተመሳሳይ ሂደት እንደሚኖር እርግጠኛ መሆን አለባቸው፡፡ በየችሎቱ የተለያየ የክስ አሰማም ዘይቤ የሚኖር ከሆነ የሂደቱ ተገማችነት ብቻ ሳይሆን የውጤቱ ተዓማኒነት ጥያቄ ላይ ይወድቃል፡፡ በሕጉ ማሳካት የታሰቡትን ዓላማዎች በሂደቱ ብዝሃነት የተነሳ ማሳካት አይቻልም፡፡ በአጠቃላይ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ከዘመኑ ጋር እንዲሄድ የማድረጉ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ እስከሚሆን ድረስ ቢያንስ በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋሉ አማራጭ የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ጉድለቶችን የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማ በጠበቀ መልኩ በትርጉም ማሟላት የሚቻል ከመሆኑም በላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መመሪያ የማውጣት ሥልጣኑን በተገቢው መንገድ በመጠቀም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚታየውን የአሰራር መዘበራረቅ በማረቅ ለክልል ፍርድ ቤቶች ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይገባል፡፡

* * *

[40] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 247(2)፡፡

# Civil Cases Hearing in the Federal Courts of Ethiopia: The Law and the Practice

*Tewodros Mihret**

**Abstract**

*One of the phases of a civil proceeding is hearing, which is a milestone to shape the extensive agruments in the written submissions and direct the overall proceeding of the case. This phase is under the full control of the court which enables it to take decisisve actions to direct the proceeding of the case. This piece argues that in addition to the failure of the law to clearly name and define this stage of a civil proceeding, the anomaly in practice prevents the achievement of the objective of the law. Further, the irregularities in practice result in wastage of resource and time of the court and the parties, not to mention the adverse effect it has on the quality of judgments. The gap between the law and the practice has made civil case proceedings unpredicatable. Thus, this piece examines the law and the praicetice with a view to forwarding recommedations.*

**Key terms**: The right to be heard, hearing, trial

∝

* Consultant and attorney-at-law.